# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የተሿሚዎች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ

የመንግስት ተሿሚዎች ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ክልል ውጭ ለመንግስት ሥራ ሲንቀሳቀሱ በፌደራል ለሚገኙ ተሿሚዎች የምግብ ብር 70 እና ለመኝታ ብር 70 በደረሰኝ የሚወራረድ፣ በክልል ለሚገኙ ተሿሚዎች ደግሞ የምግብ 70 ብር እና የመኝታ በተለያየ ሁኔታ በደረሰኝ የሚወራረድበት አሰራር እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህ የውሎ አበል አሁን ካለው የገበያ ሁኔታ ጋር ያልተጣጣመና ተሿሚዎች ለስራ ሲንቀሳቀሱ የሚያወጡትን ወጪ ሊሸፍን የማይችል በመሆኑ ጥናት ተጠንቶ የውሳኔ አስተያት እንዲቀርብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥር 3 ቀን 2004 ዓ.ም. በቁጥር ሚም30-4/ 39 ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ታዟል፡፡

በዚሁ መሰረት ጥናቱ ሀገራዊ ስታንዳርድ ለማስጠበቅ ከዘጠኙ ክልሎችና ከሁለት የከተማ መስተዳድሮች ተሿሚዎች ሊስተናገዱባቸው ይችላሉ ተብሎ ከሚገመቱ ሆቴሎች የምግብና የመኝታ የአገልግሎት ዋጋዎች ተሰብስበው በተገኘው መረጃ ላይ የየክልሉ ርእሰ መስተዳድሮች እና ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ኃላፊዎች ተወያይተው አገራዊ ስታንዳርድ እንዲኖረው በተስማሙት መሰረት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ነሀሴ 03 ቀን 2005 ዓ.ም. ም/ቤቱ ባካሄደው 54ኛ መደበኛ ስብሰባ በረቂቅ ጥናቱ ላይ ተወያይቶ በቁጥር 4/መስ54/ው223/2005 ባስተላለፈው ውሳኔ ከነሀሴ 03 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል አጽድቋል፡፡

በመሆኑም የሚኒስትሮች ም/ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ ዝርዝር መመሪያ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አውጭው ባለሥልጣን

ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 17/1/ሠ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### አንቀጽ 2

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የመንግስት ተሿሚዎች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ 2005 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

### አንቀጽ 3

### ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **በፌዴራል ደረጃ**

1.1 "የበላይ ኃላፊ" ማለት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር ደረጃ ያሉ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትሮች፣ የህዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ- ጉባኤዎች፣ የፈዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንቶች፣ የአዲስ አበባ ከንቲባና ድሬደዋ ከተማ ከንቲባዎች እንዲሁም በዚሁ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣኖች፤ ሚኒስቴር ዴኤታዎች፣ ምክትል ሚኒስትሮች፣ የፌዴራል ምክር ቤቶች ም/አፈጉባኤዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ምክትል ፕሬዘዳንቶች፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ምክትል ከንቲባዎች እና በዚሁ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣኖች፤

1.2 "ከፍተኛ ኃላፊ" ማለት በፌዴራል ደረጃ ያሉ የኤጀንሲና የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተሮች እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ የጽ/ቤት ኃላፊዎችና ምክትሎች፣ የፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ አምባሳደሮች እና

በዚሁ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣኖች፣ የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ ሥራ አስኪያጆች እና በዚሁ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣኖች ናቸው፡፡

2 **በክልል ደረጃ**

2.1 "የበላይ ኃላፊ" ማለት የክልል ርዕሰ መስተዳድር/ ፕሬዜዳንቶች፣ የክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር/ ምክትል ፕሬዜዳንቶች፤ የክልል አፈጉባኤ፡ የክልል ምክትል አፈጉባኤ፤ የክልል የጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዜዳንቶች፤ የክልል ጠቅላይ /ፍ/ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የክልል መስተዳድር የካቢኒ አባላት፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪዎች እና በዚሁ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣኖች ናቸው፡፡

2.2 "ከፍተኛ ኃላፊ" ማለት የክልል ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች፣ የክልል ኤጀንሲ፣ኢንስቲትዩት፣ ባለስልጣን እና ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የዞን ምክትል አስተዳዳሪዎች እና በዚሁ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣኖች ናቸው፡፡

2.3" በየደረጃው ያሉ የምክር ቤት አባላት" ማለት የክልል ምክር ቤት አባላት፣ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ም/ቤት አባላት፣ የብሄረሰብ ዞን ም/ቤት አባላት እና የወረዳ ምክር ቤት አባላት፣ናቸው፡፡

2.3.1 "መካከለኛ ኃላፊዎች" ማለት የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና በዚህ ደረጃ የሚሾሙ የሥራ ሃላፊዎች ፣ የወረዳ ካቢኔ አባላት፣ እና በዚህ ደረጃ የተሾሙ የሥራ ሃላፊዎች የወረዳ ጽቤት ኃላፊዎች፣ እና በዚህ ደረጃ የተሾሙ የሥራ ኃላፊዎች ናቸው፡፡

2.3.2 "ሌሎች" ማለት ደመወዝ የማይከፈላቸው የቀበሌ ተሿሚዎች፣ የመንግሥት ተቀጣሪና ተሿሚ ያልሆኑ ግለሰቦች (ቀበሌ አመራር፣ አርሶ አደር፤ ነጋዴ፤ ተማሪ፤ ወ.ዘ.ተ...) ናቸው፡፡

3 **"የቀን ውሎ አበል"** ማለት አንድ የመንግሥት ተሿሚ በአገር ውስጥ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ በዕለቱ ለመመለስ ሳይችል ሲቀር ለ24 ሰዓት ለሚያስፈልገው የምግብ እና የመኝታ ወጪ የሚከፈል አበል ነው።

4 **"የውሎ ገባ አበል"** ማለት አንድ የመንግሥት ተሿሚ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ሄዶ ዕለቱን የሚመለስ ከሆነ ለምግብ ለሚያስፈልገው ወጪ የሚከፈል አበል ነው።

5 በመመሪያው ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

https://chilot.me

## አንቀጽ 4

**የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በፌዴራልና በክልል እስከ ቀበሌ አስተዳደር እርከን ድረስ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም

## አንቀጽ 5

**የውሎ አበል ተመን**

የተሿሚዎች የቀን ውሎ አበል ተሿሚው ከመደበኛ ሥራ ቦታው ውጭ ለስራ ጉዳይ ሄዶ እለቱን ካልተመለሰ በስራ ላይ ለሚቆይባቸው ቀናት ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራትና ለመኝታ ባረፈባቸው ቦታዎች ላይ ለክልል ከተማ፣ ለዞን ከተማ፣ ለወረዳ ከተማ እና ለከተማ አስተዳደሮች በቦታ ላይ ተመስርቶ የተጠናው ውሎ አበል ለእያንዳንዱ ቀን በዚህ መመሪያ ከሰንጠረዥ 1-3 በተመለከተው መሠረት ይከፈላል፡፡

## አንቀጽ 6

## የአየር ጠባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ ለሚላክ ተሿሚ የሚከፈል የውሎ አበል

አንድ የመንግሥት ተሿሚ ለሥራ ጉዳይ የአየር ጠባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ ሲሄድ፣

1/ በአንደኛ ደረጃ የተመደበ ማለት የደመወዙ 40% የአየር ጠባይ አበል የሚከፈልበት የሥራ ቦታ ከሆነ የውሎ አበሉ 40%፣

2/ በሁለተኛ ደረጃ የተመደበ ማለት የደመወዙ 30% የአየር ጠባይ አበል የሚከፈልበት የሥራ ቦታ ከሆነ የውሎ አበሉ 30%፣

3/ በሦስተኛ ደረጃ የተመደበ ማለት የደመወዙ 20% የአየር ጠባይ አበል የሚከፈልበት የሥራ ቦታ ከሆነ የውሎ አበሉ 20% በተጨማሪ ታክሎ ይከፈለዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 7

1. የበላይ ኃላፊዎች በሚያርፉበት ቦታ እንግዶችን የሚያስተናግዱ በመሆኑ ለመንግሥት ሥራ ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ውጪ ሄደው ለሚቆዩበት ጊዜ ለሚያወጡዋቸው ልዩ ልዩ ተጨማሪ ወጪዎች በሚፈቀድላቸው ውሎ አበል ላይ በተጨማሪ፣
   - በም/ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ ለተሾሙ የሥራ ኃላፊዎች ብር 3000/ ሶስት ሺህ ብር/፣
   - ለሚኒስትሮች ብር 2000/ ሁለት ሺህ /ደረሰኝ የማይቀርብበት ለመስተንግዶ ወጪ ተፈቅዷል፡፡
   - የክልል ፕሬዚደንቶች የቀን ውሎ አበል የምግብና የመኝታ እስከ አራት ኮከብ ደረጃ ባላቸው ሆቴሎች በሚያቀርቡት ደረሰኝ መሰረት የሚሸፈን ሲሆን በተጨማሪም ብር 2000/ ሁለት ሺህ ብር/ ደረሰኝ የማይቀርብበት ለመስተንግዶ ወጪ ተፈቅዷል፡፡
   - ሆኖም ለመስተንግዶ የተፈቀደው ወጪ ስራ ላይ ካልዋለ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
2. ከአብዛኞዎቹ የበላይ ኃላፊዎች ጋር ልዩ ጥበቃና ሾፌር አብረዋቸው የሚጓዙ በመሆኑና ለኃላፊዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከኃላፊዎቹ ተለይተው መንቀሳቀስ ስለማይችሉ ፣ከበላይ አመራሮች ጋር የሚንቀሳቀሱ ሾፌሮችና የጥበቃ ኃይሎች በደመወዛቸው መጠን የቀን የምግብ አበል በገንዘብ እንዲሰጣቸውና የመኝታ ወጪያቸው ግን ኃላፊዎቹ በሚያርፉበት ሆቴል የባለ አንድ አልጋ ክፍል መኝታ ወጪ በደረሰኝ የሚሸፈን ይሆናል፡፡
3. ለበላይ ኃላፊዎች እስከ 4 ኮከብ ደረጃ ባለው ሆቴል የመኝታ ወጪ በሚቀርበው ደረሰኝ መሰረት የሚሸፈን ሲሆን የምግብ ወጪያቸው ግን ደረሰኝ የማይቀርብበት ሆኖ ለከተማው በተመደበው የቀን አበል መሰረት ተሰልቶ ይፈጸማል፡፡

4. የውሎ አበል ተመን የተመሠረተው ከሙሉ የአንድ ቀን የውሎ አበል ተመን ውስጥ 10% ለቁርስ፣ 25% ለምሣ፣ 25% ለእራትና እና 40% ለአልጋ በመመደብ ነው፡፡
5. አንዳንድ የክልል ከተሞች እና የዞን ከተሞች የወረዳ ከተማ መቀመጫዎች ሆነው የሚያገለግሉ በመሆኑ ለክልሉ ወይም ለዞን ከተማው የተመደበው የቀን ውሎ አበል ተመን ለወረዳ ከተማው ጭምር የሚያገለግል ይሆናል፡፡
6. አዲስ የክልል/ዞን/ወረዳ/ከተማ ሲሰየም ወይም ሲከፈት የክልል መንግሥታት ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 8
## ስለተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች የተሻሚዎች የአገር ውስጥ የቀን የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያዎች፣ ሠርኩላሮችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## አንቀጽ 9
## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

**ይህ መመሪያ ከነሀሴ 3 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡**

# የውሎ አበል ተመን

## ለክልል ዋና ከተሞች እና ለሁለት የከተማ መስተዳድሮች የቀን ውሎ አበል ክፍያ

### ሠንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | የከተሞች ስም | ለበላይ ኃላፊዎች | ለከፍተኛ ኃላፊዎች | በየደረጃው ያሉ የክልል ም/ቤት አባላት | | መካከለኛ ሀላፊዎች □□ | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | I | II | | |
| 1 | ባህርዳር | 690 | 575 | 218 | 176 | እንደሚከፈላቸው ወር ደመወዝ አበሉ የሚያርፉበት ይከፈላቸዋል | 134 |
| 2 | አዲስ አበባ /ፊንፊኔ | 755 | 575 | 206 | 165 | | 124 |
| 3 | ድሬዳዋ | 685 | 540 | 214 | 171 | | 128 |
| 4 | ሐዋሳ | 705 | 590 | 202 | 192 | | 182 |
| 5 | ሐረር | 610 | 480 | 198 | 157 | | 116 |
| 6 | መቀሌ | 650 | 515 | 225 | 176 | | 138 |
| 7 | ጋምቤላ | 565 | 450 | 191 | 174 | | 157 |
| 8 | ሰመራ | 575 | 535 | 141 | 126 | | 111 |
| 9 | ጅጅጋ | 595 | 515 | 189 | 160 | | 131 |
| 10 | አሶሳ | 500 | 430 | 177 | 144 | | 111 |

- I. የክልል ምክር ቤት አባላትና፣ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ም/ቤት እና፣ የ ብሄረሰብ ዞን ም/ቤት አባላት
  II. የወረዳ ምክር ቤት አባላት

| ተ.ቁ | የክልሉ ስም | የከተሞች ስም | ለበላይ ኃላፊዎች | ለከፍተኛ ኃላፊዎች | በየደረጃው ያሉ የክልል ም/ቤት አባላት | | መከከለኛ አመራር | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | I | II | | |
| | | አሰላ፣ ሮቤ፣ፍቼ | 510 | 410 | 179 | 149 | | 124 |
| | | ጊምቢ፣ ጂማ፣መቱ፣ ወሊሶ፣ ሻምቡ | 535 | 450 | 179 | 149 | | 124 |
| | | ደምቢዶሎ | 535 | 450 | 106 | 102 | | 124 |
| 8 | አማራ | ፍኖተሰላም | 490 | 385 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ላሊበላ | 665 | 525 | 218 | 176 | | 134 |
| | | ደብረማርቆስ | 420 | 360 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ደብረታቦር | 400 | 340 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ወልዲያ | 435 | 355 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ደብረብርሃን | 430 | 370 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ደሴ | 520 | 438 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ጎንደር | 715 | 515 | 218 | 176 | | 134 |
| | | ከሚሴ | 380 | 330 | 192 | 157 | | 122 |
| | | እንጅባራ | 395 | 335 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ኮምቦልቻ | 588 | 435 | 192 | 157 | | 122 |
| | | ሰቆጣ | 380 | 330 | 192 | 157 | | 122 |

## ለወረዳ ከተሞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ

የወረዳ ከተሞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ የተመሰረተው ለመንግስት ሠራተኞች በ2004 ዓ. ም. ተፈቅዶ ስራ ላይ በዋለው የቀን ውሎ አበል ተመን ለየወረዳው በተመደበው ምድብ ላይ ተመስርቶ ሲሆን አመዳደቡም፤

### ሀ. ለበላይና ከፍተኛ ኃላፊዎች

በክልል የወረዳ ከተሞች ለበላይና ለከፍተኛ ኃላፊዎች ማረፊያ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ሆቴሎች ይኖራሉ ተብሎ ስለማይጠበቅ እና አብዛኞቹም ተጂሚዎች በዞን ከተሞች በሚገኙ ሆቴሎች እንደሚጠቀሙ ታሳቢ በማድረግ የወረዳ ከተሞች አበል የተለያየ የቦታ ላይ ተመን ሳይስፈልገው ለሌሎች ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ከብር 3816 በላይ ላሉት የተፈቀደው አበል ላይ ለምግብ 50%፣ ለመኝታ 50% በመጨመር ፤

### ለ . በየደረጃው ያሉ የክልል ምክር ቤት አባላት

I. የክልል ምክር ቤት አባላትና የደቡብ ብሔር ብሄረሰብ ም/ቤት አባላትና የብሄረሰብ ዞን ም/ቤት አባላት ለመንግስት ሠራተኛው በቦታ ላይ ተመስርቶ ለየከተሞቹ በደመወዝ ደረጃ ከብር 3816 በላይ ላሉት የፀደቀውን የቀን ውሎ አበል ተግባራዊ ማድረግ ፣

II. የወረዳ ምክርቤት አባላት ለመንግስት ሠራተኛው በቦታ ላይ ተመስርቶ ለየከተሞቹ በደመወዝ ደረጃ በብር 2249 እስከ ብር 3816 ላሉት የፀደቀውን የቀን ውሎ አበል ተግባራዊ ማድረግ ነው ፡፡

### ሐ. መካከለኛ ኃላፊዎች

መካከለኛ ኃላፊዎች በሚከፈላቸው የወር ደመወዝ ልክ ለመንግስት ሠራተኞች በቦታ ላይ ተመስርቶ ለየከተሞቹ የፀደቀውን የቀን ውሎ አበል ለነሱም ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

### መ. ሌሎች

"ሌሎች" በሚለው ስር ለተመለከቱት ለመንግስት ሠራተኛው በቦታ ላይ ተመስርቶ ለየከተሞች በደመወዝ ደረጃ እስከ ብር 2248 ላሉት የፀደቀውን የቀን ውሎ አበል ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን ዝርዝሩ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡

https://chilot.me

<u>**ሠንጠረዥ 3**</u>

| ተ.ቁ | የወረዳ ስም | የከተሞች ስም | ለበላይ ኃላፊዎች ለከፍተኛ ኃላፊዎች | በየደረጃው ያሉ የክልል ም/ቤት አባላት | | መካከለኛ ሀላፊዎች | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | I | II | | |
| 1 | አፋር | ምድብ 1 | 338 | 169 | 138 | እንደሚከፈላቸው የወር ደመወዝ መጠን ለመንግስት ሠራተኛው የተፈቀደው አበል የሚያርፍበት ይከፈላቸዋል | 107 |
| | | ምድብ 2 | 242 | 121 | 101 | | 91 |
| 2 | አማራ | ምድብ 1 | 326 | 163 | 135 | | 107 |
| | | ምድብ 2 | 224 | 112 | 102 | | 92 |
| 3 | ቤንሻንጉል | ምድብ 1 | 300 | 150 | 126 | | 102 |
| | | ምድብ 2 | 214 | 107 | 96 | | 85 |
| 4 | ጋምቤላ | ምድብ 1 | 282 | 141 | 128 | | 115 |
| | | ምድብ 2 | 202 | 101 | 92 | | 83 |
| 5 | ደቡብ | ምድብ 1 | 342 | 171 | 147 | | 123 |
| | | ምድብ 2 | 214 | 107 | 100 | | 98 |
| 6 | ኦሮሚያ | ምድብ 1 | 342 | 171 | 147 | | 123 |
| | | ምድብ 2 | 198 | 99 | 96 | | 93 |
| 7 | ትግራይ | ውቅሮ፣ዓብይአዲ፣አላማጣ፣ሽራሮ፣ ኮረም፣ዓድዋ | 326 | 163 | 134 | | 105 |
| | | አፈላ፣ራያአዘቦ እና ለተቀሩት ወረዳ ከተሞች | 318 | 159 | 130 | | 101 |
| 8 | ሶማሌ | ለሁሉም የወረዳ ከተሞች | 250 | 125 | 107 | | 89 |